# ኣምባገነንና ምርጫ ኣብረው ኣይሄዱም !

ሰሞኑን የኢሀዴግ መሪው ጠቅላይ ሚኒስትር ተብየው ለገሠ ("መለስ") ዜናዊ "በትግራይ ምርጫ እንደምናሸንፍ የታወቀ ነው፥ ጭንቀታችን ዴሞክራሲያዊነቱን ማረጋገጥ ነው" ማለቱን ሪፖርተር በጥቅምት 28 ቀን 1997 ዒ.ም እትሙ ዘግቦት ይገኛል ። ይህ አዋጅ ኢህአዴግ ባዘጋጀውና በሚቆጣጠረው የምርጫ ትርኢት ውስጥ ተሳትፈን ለውጥ እናመጣልን ለሚሉት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሁሉ እንዲያውቁት ሆን ተብሎ የተነገረ ኣምባገነናዊ መልእክት በመሆኑ ጉዳዩ ይመለከተናል የሚሉ ወገኖች የመልእክቱን ኣደገኛ ገጽታ በጥልቀት ቢመረምሩት ይበጃል እንላለን ። በግልጽና ባጭር አነጋገር ተወዳድረን እናሸንፋለን ብላቹ ከልብ አስባቹ ከሆነ ፤ አይምሰላቹህ አትልፉ ፥ ጭንቀታችን ስልጣናችንን በመጠበቅ ለሚተባበሩን ስንል ዴሞክራት መምሰል ስላለብን ኣንድ=ሁለት ወንበር እንለቅላቹህ ይሆናል የሚል መልእክት እየተላለፈላቸው መሆኑ ሊገነዘቡት
ይገባል ።

ገና ምርጫው ከመላሄዱ በፊት ማሸነፉን ለማሳወቅ፥ አቶ ለገሠ "በትግራይ ምርጫ እንደምናሸንፍ የታወቀ ነው" ይላል ። መልእክቱ በሚገባ ደርሶናል ። ነገር ግን በትግራይ ብቻ ሳይሆን በመላው አገሪቱ መጪውን ምርጫ እንደሚያሸንፍ የምናውቀው ዛሬ ሳይሆን ገና ከጥዋቱ የአገሪቱን የምርጫ ቦርድና ደንቡ ለብቻው በሚመቸው መንገድ አስተካክሎ ሲፈጥር ነው። ባለፈው ምርጫም ኣሸነፍኩ ያለው በዚሁ የቅጥፈት ዘዴ ካልሆነ የትኛው ህዝብ ደግፎት ነው ? ያ ብቻም አይደለም ፡ ሁኔታዎች አሁን ባሉበት መልክ እንዲቀጥሉ ከተውናቸው ገና የሚቀጥሉት ብዙ ምርጫዎችንም እንደሚያሸንፍ ዛሬውኑ በድፍረት መናገር እንችላለን ። ይህን የምንለው ያለበቂ ማስረጃ ኣይደለም ።

በምርጫ ማሸነፍ ወይም መሸነፍ የሚታወቀው፥ ኣቶ ለገሠ እንዳወጀው ከምርጫ በፊት ሳይሆን፥ ምርጫው ሲፈጸም ቢሆንም የእውነት ምርጫ ለማካሄድ የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎች በቅድሚያ ተሟልተው መገኘት ይኖርባቸዋል። እነዚህ ቅድመ=ሁኔታዎች ደግሞ ነፃ የምርጫ ቦርድና ደንቡ ፥ ነፃ የግልና የህዝብ መገናኛ ብዙኃን ፥ ነፃ የምርጫ ታዛቢ አካል እንዲሁም የመደራጀት፣ የመንቀሳቀስና ሓሳብን በነፃ የመግለጽ መብት በተግባር መረጋገጥ ፥ . . . ወዘተ በቅድሚያ መሟላትን ይጠይቃል ። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ግን እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች አላሟላም፣ እንዳይሟላም ሆን ብሎ ያገደ ኣፋኝ መንግስት ኣለ። ይህ እስካልተሟላ ደግሞ በምርጫ ስለ ማሸነፍም ሆነ መሸነፍ ማውራት ከየትኛውም ኣቅጣጫ ሲታይ ቢይንስ እውነታን ያልተላበሰ ወሬ ይሆናል። ከዚህ ተነስተን የአቶ ለገሠ የእናሸንፋለን ዲስኩር ስናየው ህዝቡን እንደተለመደው ለማወናበድ፥ ተቃዋሚውን የምርጫ ውድድር ያለ ይመስል ለመከፋፈል፥ እንዲሁም በመፍረስ ላይ ያለው የቅጥረኛውና ኣድርባዩ ሞራል ለመጠገን ወቅቱን ጠብቆ የተሰነዘረ ስሌታዊ መልእክት መሆኑ እንገነዘባለን ።

ኣራዳው አቶ ለገሠ የምርጫ ኣድማሳዊ ቅድመ ሁኔታዎች ተሟልተው በፕሮግራማችን መሰረት እኩል ተወዳድረን እናሸንፋለን አላለም ። ኣስልቶ ያለን "ትግራይ ውስጥ ምርጫ እንደምናሸንፍ የታወቀ ነው"ና እወቁት ነው ። መልሳችን ደግሞ እንደድሮው አዎ ታሸንፋለህ ! ብቻህን ከሮጥክ፣ በፈለገው ሰዓት ብትደርስ፥ ለዛውም የራስህን ቅጥረኛ ዳኛ ኣስቀምጠህ፥ ሁሉ ጊዜ አሸናፊ አንተ እንደምትሆን የምንጠራጠርበት ምክንያት አይኖርም ነው ። ይህንን እውነታ

የትግራይ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ኣሳምሮ ያውቀዋል ። ባለፈው ምርጫ ታዛቢዎች የነበሩት የምእራቡ ዓለም መንግሥታትም ኢህአዴግን የመሰለ ታዛዥ አገልጋይ እንደማያገኙ በማወቅ ዓይናቸውን ለመጨፈን ቢመርጡም ከራሱ ጋር ተወዳድሮ አሸነፍኩ እንዳለ አሳምረው ያውቃሉ። ካስፈለገ በ1995 ዓ/ም/ፈ/ ታትም የወጣው የኖርዌጇኖቹ ዘገባ መመልከት ነው። ኣቶ ለገሠና ጃንጥላው ኢህአዴግ በተደጋጋሚ ያሳዩን በዴሞክራሲ የማፌዝ ተግባራቸው ባጠቃላይ ይህንኑ ቢመስልም፣ ለተጨማሪ ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ ባለፉት ዓመታት በመርጫ ዙርያ የታዩት ክስተቶችን ቀንጨብ አርገን በማቅረብ "... እንደምናሸንፍ የታወቀ ነው " ተብሎ ያለ ሓፍረት የተሰነዘረው ድንፋት ይዘቱን እናብራራለን ።

በ1994 ዓ.ም በተደረገው የኢህአዴግ "ነፃ" ምርጫ በትግራይ ውስጥ ያለ ምንም ውድድርና የምረጡኝ ዘመቻ በአቶ ለገሠ ዜናዊ የሚመራው ህወሓት አባላቱን ከየጣቢያው በትእዛዝ ማስመረጡ ይታወሳል ። በዚህ ምርጫ ወቅት የዛላንበሳ ከተማ በሻዓቢያ ጦር ፈራርሳ ፥ የዛላንበሳ ከተማ ህዝብ በየዋሻውና በየጣሻው ተበታትኖ መከራን ሲጋፈጥ ፥ በምርጫው ዕለት በዛላንበሳ ግንባር የወገን ሰራዊት ዳር ድንበሩን ለማስከበር ከጠላት ጋር ትንቅንቅ ተያይዞ በመዋደቅ ላይ እንደነበረ እየታወቀ፥ ምርጫ ካልተካሄደባት ዛላንበሳ አምባሳደር አውዓሎም ወልዱ ተመረጡ ተብሎ ፓርላማ ውስጥ መቀመጫ ሲይዙ ምርጫ ቦርድ ተብዬው የምርጫ ሕግና ደንብ ተጣሰ ብሎ ውድቅ ሲያደርገው አላየንም ፥ አልሰማንም ። የአቶ አውዓሎምን የዛላንበሳ ህዝብ ከነበረበት ሁኔታ አንጻር አነሳን እንጂ በዛ የምርጫ ተብዬ ወቅት ትግራይ ውስጥ ምረጡኝ ብሎ በወጉ መራጩ ህዝብ ፊት ቀርቦ የተመረጠ አንድም የህዝብ ወኪል እንዳልነበረ ግልጽ ነው ።

ከዚህ በተያያዘ ምክንያትም ሌሎቹ ተመራጭ የተባሉት እነ ወ/ት አረጋሽ አዳነ ፥ አቶ ገብሩ አሥራት ፥ አቶ ተወልደ ወልደማርያም ፥ አቶ አውዓሎም ወልዱ ፥ አቶ ሥዬ አብርሃ ፥. . . ወዘተ ከአቶ ለገሠ ዜናዊ ቡድን ጋር በተጣሉ ዕለት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከተወካዮች ምክር ቤትና ከፌደሬሽን ምክር ቤት በተራ ኣምባገነናዊ ሴራ ሲባረሩ አይተናል ። ይህ አሠራር በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሕግ=ስርአት መሰረት መመረጥና መምረጥን የሚያመላክት ፍንጭ አይታይበትም ። በ'ፍትሕ ሃላፊ' የሚመራ ገለልተኛ አካል እየተባለ የአቶ ለገሠ መመጻደቀያ የሆነው ምርጫ ቦርድም፥ ሕገ መንግሥት የጣሉብኝ ሓላፊነቴ በጠራራ ፀሐይ ተነጥቅኩኝ ብሎ መብቱን ለማስከበር ሕግ አፍራሾችን ለይስሙላ እንኳ ሲከስ ወይም ፍርድ ቤት ማቅረቡን አልሰማንም ። የሰማነው በተቃራኒው ነው ። ከሕግ አፍራሾች ከነኣቶ ለገሠ ጎን ቆሞ የመራጩን (ምርጫ ከተባለ) ህዝብ ውክልና ለመግፈፍ የተዶለተው ሴራ አካል ሆኖ ሲያቀነባብር ነበር የታዘብነው ።

ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ ባለበት ምርጫ ተካሂዶ ቢሆን ኖሮ ይህ ክስተት ሊታይ ይችል ነበር ወይ ብለን ብንጠይቅ፥ መልሱም ጭራሽ አይሆንም ነው ። ምክንያቱም ገለልተኛ ምርጫ ቦርድ በመጀመሪያ ደረጃ ከህዝብ የመነጨውንና በሕግ የተሰጠውን መብት ለማስከበር ሴረኞችን ሕግ ፊት የማቅረብ ሓላፊነቱን ይወጣል፤ በዚህ መንገድም ለህዝብ ያለው ታማኝነትን ለማሳየት የሞራል ብቃትም ስለሚኖረው ህዝባዊ ወገናዊነቱን ያስመሰክራል ፥ ከተወቃሽነትም ሆነ ተጠያቂነት ይድናል ። በሁለተኛ ደረጃ በቃለ ማህላ የተረከበውን የህዝብ አመኔታ አስከብሮ ስለሚዘልቅ የህዝብ ተወካይን ከወካዩ ህዝብ በስተቀር ማንም ባሻው ጊዜ መሻር እንደማይችል ሕግን ተመርኩዞ ማገድ ይችላል ። ሶስተኛውና ዋነኛው ግን ከመጀመሪያው ጀምሮ ምርጫ በግለሰቦች ፍላጎት ሳይሆን በህዝብ ፍላጎት እንዲመራ ህዝብን ተገን ኣድርጎ ኣድማሳዊ ደረጃው ይጠብቅ ዘንድ መንገድ ማስያዝ ይችላል። አለመታደል ሆነና ግን ምርጫ ቦርዱ ገለልተኛ መሆኑ ቀርቶ አምባገነን መሪዎች ለራሳችው አገልግሎት እንዲመች አድርገው ያዋቀሩት ቡድን ስለሆነም የህዝቡ ድምጽ ኣምባገነኖቹና ኣድርባዮቹ ሲገለገሉበትና ሲቀልዱበት ለማየት በቅተናል ።

ይህ ብቻም አይደለም፤ ባለፈው ዓመት በተምቤን አውራጃ ውስጥ የዓቢይ ዓዲ ከተማ ህዝብ የመብራት ፥ የውኃ ፥ የባንክ ፥ የስልክ . . . ወዘተ አገልግሎቶች እንዲሟሉልን ለኣመታት ስንማጸን ብንቆይም ሰሚ ጆሮ አጣን በማለት ሰላማዊ ሰልፍ ለመውጣት ካስፈቀደ በህዋላ የህወሓት ባለሥልጣናት ሰላማዊ ሰልፉን ለማስቀም ሞክረው በህዝቡ ጽናት ሳይሳካላቸው መቅረቱና ህዝቡም ፈንቅሎ ሰላማዊ ሰልፍ መውጣቱ ይታወሳል ። በዚህ ምክንያትም የህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎች

ህዝቡን ከፋፍለው እርስ በርሱ እንዲባላና ጥያቄው በሕብረት እንዳያቀርብ ለማረግ ሰፊ ዘመቻ ከፍተው ቁም ስቅሉን ሲያሳዩት መክረማቸው ይታወቃል ። ህዝብ ያገለግሉኛል ብሎ የመረጣቸው ኣስተዳዳሪዎቹን እንዲያወርድ ለማስገደድ ከፍተኛ የማስፈራራት እርምጃ መውሰዳቸውን አይተናል ። ህዝቡ ባቋሙ በመጽናቱና የሚፈልጉትን እንደለመዱት በማስፈራራት ለማስፈጸም እንደማይችሉ ሲያሳያቸው አምባገነናዊ ባሕሪያቸው እርቃኑ ወጥቶ የህዝብ ተመራጩችን ከህዝብ ፍላጎት ውጭ በባለሥልጣናቱ ትእዛዝ ኣንድ ባንድ በተናጠል በማባረርና ባመራሩ ታማኞች መተካታቸው ገሀድ ሆኖ ታይቷል ። እንዲህ ዓይነት የህዝብ መብት ረገጣ ባፈጠጠና ባገጠጠ መልኩ ሲፈጸም "ገለልተኛ" የተባለው ምርጫ ቦርድ ጣልቃ ገብቶ የህዝብን ድምጽ እንዲከበር ሲሟገት አልታየም ።

ከዚህም ሌላ ለገሠ ዜናዊ በተለመደው ኣስመሳይ አንደበቱ "ጭንቀታችን ዴሞክራሲያዊነቱን ማረጋገጥ ነው" በማለት የጨመረው ሐረግ ነው ። ለመሆኑ አምባገነኖች ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ለማካሄድ የሚችሉት በምን ተአምር ነው ? የሚል ጥያቄ እንድናነሳ ያስገድደናል ። በመሰረቱ ኣምባገነንነትና ምርጫ ኣብረው ኣይሄዱም፤ ጸር ናቸውና። ጸረ=ህዝቡ ለገሠና ተበዳዩ ህዝብ ሆድና ጀርባ ናቸው። ስለዚህም የኢህአዴግ ምርጫን አስመልክቶ ያለፉት ኣሳፋሪ ልምዶች ምን እንዳስተማሩን ከዚህ በላይ በዝርዝር ለማስቀመጥ ሞክረናል ። መጪው ምርጫ ደግሞ የተለየ ሊሆን የሚችልበት ልዩ እድገት እስከዛሬ ለማየት አልቻልንም ። ኣሁንም ምርጫ ቦርድ የራሱ ፍጡር ፥ የምርጫ አዘጋጅ ራሱ ፥ የምርጫ ውጤት አሻጊና ቆጣሪ ራሱ ነው። "ካሮትና በትር" የሚሉት ዘይቤ እየተጠቀመ፥ ለህዝብ የመጣውን እርዳታ፥ ማዳበርያና ብድር የምርጫ ካርድ መግዣ ሲያደርገው፣ ካድሬው ብረት አንግቦ መራጩን ሲያስገድድና ታዋቂ ተወዳዳሪዎች ሲያፍን፥ በመንግሥት መዋቅር የተቀመጡ የመንግሥት ቅጥር ሠራተኞች ከሥራቸው እንዳይባረሩ በመስጋት ከሂሊናቸው ጋር እየታገሉ የኢህአዴግ አሸናፊነት እንዲረጋገጥ ለመሥራት በተገደዱበት ሁኔታ ውስጥ "ጭንቀታችን ዴሞክራሲያዊነቱን ማረጋገጥ ነው" ማለት ትርጉም የለሽ ቀልድ ብቻ ሳይሆን የቅጥፈትም ቅጥፈት ነው ።

የምርጫ ዴሞክራሲያዊነት ለማረጋገጥ ከተፈለገ ትክክለኛው መንገድ አንድ ብቻ ነው ። ይኸውም ምርጫ ቦርዱ ገለልተኛ ሆኖ ወይም በጋራ የተመሰረተ፥ ሕገ=ደንቡም በዚህ መንፈስ የተደነገገ ሲሆንና፥ አማራጭ ፕሮግራም ይዘው ለምርጫ ህዝብ ፊት ሊቀርቡ የሚችሉ እንደ ት.ዴ.ት ያሉ ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች በምርጫ ተሳታፊ እንዲሆኑ በድፍረት መቀበል ነው ። ያኔ ነው የህወሓት/ኢህአዴግ ፕሮግራም በህዝብ ይደገፋል = አይደገፍም የሚታየው። በፕሮግራሙ እኩል ሜዳ ላይ ተወዳድሮ ህዝብ ይሁንታውን ያለመሸማቀቅ ሲሰጥበት ፥ ካሸነፈ ለማሸነፉ እውቅና ማግኘት ይችላል ። ካልሆነ ግን የህዝብ ድምጽን አፍኖ፥ ተወዳዳሪ ድርጅቶች በተለያየ ዘዴ ኣግዶ፥ ባዶ ሜዳ ላይ ሳይወዳደር አሸነፍኩ ብሎ ቢኮፈስ ኣምባገነንነት ከማረጋገጥ በቀር ተቀባይነት አይኖረውም ። ት.ዴ.ት.ም ይህንን መሰል በህዝብና ባገር ላይ የሚደረገውን ቀልድም ቅጥፈትም አጥብቆ ይኮንናል፤ እስከመጨረሻም ይታገለዋል ።

ከላይ የተጠቀሱት ዘርፈ ብዙ የአምባገነኖች የተለመዱ ገጸ ባሕሪያትን ግምት ውስጥ አስገብተን ያቶ ለገሰ ኣስመሳይነት ስናጤን ለየት ያለ ኣሳፋሪ ጠባይ እንገነዘባልን። ይኸውም ከህዝብ መደበቅ ወይም ህዝቡን ኣርቄልኝ ማለቱ ነው። ዛሬ ህዝብ ማህል ተገኝቶ ፊትለፊት ሓሳቡን ለመግለጽ ያልደፈረና ፥ መረጠኝ ወይም ይመርጠኛል የሚለውን ህዝብ አጠገቤ እንዳይደርስ አርቄልኝ የሚለው ለገሠ ዜናዊ ስለ ምርጫው ዴሞክራሲያውነት ተጨነኩ ሲለን ኣይን ኣውጣ ... ከማለት ኣንመለስም። በሚያስተዳድረው አገር ውስጥ የተግባሩ እስረኛ ሆኖ ምስሉን በቴሌቪዥን መስኮት ብቻ እያሳየ የሚኖር መሪ ሰምተንም ኣይተንም ኣናውቅም። ከዚህ ዓይነት መሪ ተብዩ አምባገነን አንደበት በምርጫ አሸንፋለሁ የሚል ድምጽ ሲሰማ ፥ እንዴት ማሸነፍ እንደሚችል አሁንም ያልተገነዘቡ ወይም ተገንዝበው ምን ከፋን የሚሉ ወገኖች መኖራቸው ስናይ ግን ሳይገርመን አልቀረም ።

በዚህ ምክንያትም ለገሠ ዜናዊና ቡድኑ ከዚህ በፊትም ሆነ አሁን በምርጫ ሽፋን ሥልጣን

ላይ ለመቆየት የሚጠቀሙበት ዘዴ ላልተገነዘቡ ሁሉ ግልጽ ማድረግ ሊያስፈልግ ነው ። ከሃዲው ለገሠ ገና ወደ ሥልጣን ለመውጣት ሲያኮበኩብ የኢትዮጵያ ህዝብን ሳይሆን የኤርትራው ሻዓቢያን ተገን አድርጎ ነበር ። ለዚህ ውለታም ኤርትራን ሁሉንም ቀድሞ በኣደባባይ አስገነጠለ ፤ ኢትዮጵያን ተፈጥሮአዊ ፥ ታሪካዊና ህጋዊ የባሕር በሯን አሳጣት ፤ 144 ሺ ኢትዮጵያዊያን ንብረታቸውን ተነጥቀው ሲባረሩ ውሸት ነው ፥ አልተደረገም ብሎ ጥብቅና ቆመ (EPRDF NEWS BULLETIN, August 30, 1991 ይመልከቱ) ፥ ኤርትራ በዓለም 13ኛ ቡና አምራች አገር እንድትባል አደረገ ፥ ታሪካዊ ባንዴራ እንደሌለን ሁሉ የኤርትራ ባንዲራ ታጥቆ ጨፈረ አስጨፈረ ። ይህ ሁሉ በደል በኢትዮጵያ ላይ ሲያወርድ ገፈት ቀማሹ የትግራይ ህዝብ እንደማነኛውም ኢትዮጵያዊ አምረሮ ተቃወመ ፥ ሰላማዊ ሰልፍም ወጣ ። ይሁን እንጂ የለገሠ ቅጥረኞች ደበደቡት ፥ አሰሩት ፥ ገደሉት ተቃውሞውንም አኮላሹት ። በዚህ ወቅት ነበር በኢትዮጵያ ትልቁ ዘመናዊ እስርቤት ትግራይ ውስጥ በሽሬ ከተማ መገንባት የተጀመረው ። በዚህ የአፈና ድርጊት ያልተንበረከከው የትግራይ ህዝብ ትግሉን ቀጥሎበት የትግራይ አስተዳዳሪዎች (እነ አቶ ገብሩ አሥራት ፥ ወ/ሮ አረጋሽ አዳነ) ሳይቀሩ እንደድሮው መግዛት አቅቷቸው የህዝቡን ዋይታ ማዳመጥ ጀመሩ ። በዚህ ማኸል የባድመ ጦርነት ተቀሰቀሰ ። የኢትዮጵያ ህዝብ በአንድነት ቆሞ ወራሪውን ሻዓቢያን ለመመከት ወደ ትግራይ ሲተም የትግራይ ህዝብ እንደወትሮው ሕፃን ሽማግሌው በደጀንነት ወጣቱ ደግሞ በግንባር ቀደምትነት በመሰለፍ የማያዳግም ድል በማስመዝገብ ላይ እያለ ነበር ለገሠ ዜናዊ ድሉን ያስነጠቀው ። በለገሠ ክህደት ነው የ50 ሺ ወጣት ሕይወት የተከፈለበት ድል ውኃ እንዲበላው የተደረገው ።
ከዚህ ቁጭት በመነሳት ነበር " ከጦርነት መልስ ወደ መለስ " የሚል መፈክር ህዝቡ ያስተጋባው። መልእክቱ የመከራችን ማእከል "መለስ" ነውና በጦርነትም ቢሆን እናጥፋው የሚል መሆኑ ግልጽ ነበር ። ከዚህ በህዋላም ነበር ይህ "መሪ" ድሮ ተዝናንቶ ሲንጎራደድበት ከነበረ ትግራይ ከህዝብም ጭምር መደበቅ የጀመረው ። የትግራይ መሬት ዛሬ እሱን የማይምር የቁጣ ወላፈን እንደሚንቦገበግበት በመገንዘቡ በታንክና ትግርኛ በማይሰሙ ፈጥኖ ደራሾች ተከቦ የትግራይ ከተሞችን የሚረግጠው ።

በዓይን የሚታየው ፥ በጆሮ የሚሰማው ፥ በሂሊና የሚዳሰሰው እውነታ ይህ ሆኖ እያለ አቶ ለገሠ "በትግራይ ምርጫ እንደምናሸንፍ የታወቀ ነው" እያለ ሲያቅራራ ይሰማል። ታዲያ የህዝቡና ያቶ ለገሠ ሁኔታ እንዲያው ጭድና እሳት ሆኖ እያለ፥ መልእክቱ ተወደደም ተጠላ አሸናፊው እኔ ነኝ የሚል መሆኑ ግልጽ አይደለም እንዴ ? መልእክቱ ህዝብን አስፈራርቼ ፥ ሳጥኖቹን ገለባብጬ ታዛቢዎችን አጭበርብሬ አሸንፋለሁ፤ ክርክር ተነስቶ ለፍርድ እንቅረብ ቢባልም ምርጫ ቦርዴን ይዤ እንዳሸነፍኩ አስፈርዳልሁ ብሎ ሳይዋሽ ሃቁን ይናገር ካላልን በስተቀር ቁርጡን ሊገባን በሚችል ቋንቋ እየነገረን ነው ። ኣዲስ ኣበባን ጨምሮ ኣንድ/ሁለት ከተሞች ማሸነፍ ተችለዋል እኮ የሚሉ ወገኖች ኣሉ። መልሳችን ታዲያ እርዳታና ብድር ኣቀባዮቹ ኣታጭበርብራቸው ብሎ ከመለመን ኣልፎ ገጠሩን ሄዳችሁ ሞክሩት ነው።

ይህን የአቶ ለገሠ ዓይን አውጣ አምባገነናዊ ተንኮልን እስካሁን ያልተረዳ ሰው ካለ ለተለያዩ ምክንያቶች አውቆ ዓይኑን የጨፈነ ብቻ መሆን አለበት ። ኢትዮጵያ ዘግናኝና አሳፋሪ ሁኔታ ውስጥ እንዳለችና ከዛም ወደባሰ ሁኔታ ልትገፋ እንደምትችል ሊቀበል ያልፈለገ ፥ አውቆ የተኛ ነገ በቃጠሎ ማህል ሲቀሰቀስ እሚለው የሚጠፋው ፍጡር መሆን አለበት ። ተወደደም ተጠላ ይህ ሥርዓት የሚመራው የአገሪቱን ህልውና ሊያስጠብቅ በማይችል፥ ነገ እንደድሮው መግዛት ካልቻለ ጥሎ ሊሸሽ በተዘጋጀ፥ ህዝብ የራቀው አምባገነን መሆኑ ሁሉም ዜጋ ሊያውቀው ይገባል ። በተጨማሪም የዚህ ሥርዓት የጥፋት ኣቅጣጫ ሥርዓቱንና አማኞቹንም ጭምር ሳይቀር ይዞ ሊጠፋ የሚችል መሆኑ ሁሉም ሊገነዘቡት ይገባል ። ስለዚህም ሥርዓቱን በወቅቱ በሰላማዊ መንገድ ለመለወጥ የሚደረግ ትግልን በማፋጠን አምባገነንነትን ከስሩ ለማጥፋት ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦ ማበርከት ይጠበቅበትል ።

አምባገነንነት ተመልሶ እንዳይመጣ በሩን ለዘላለሙ ለመዝጋት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊያን ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) መሰረቱን ኣስቀምጠዋል። ከረጅም ጊዜ ትግልና ጥናት በህዋላ የኢትዮጵያ መሠረታዊ ችግሮች የነለገሠ ፀረ=ህዝብና ፀረ=ሀገር አገዛዝን ብቻ

ሳይሆን ህዋላ ቀርነትንና መጥፎ ኣሰራርን ተጠቅመው ለወደፊት ሊመጡ የሚችሉ አምባገነኖችም እንዳይኖሩ ለማድረግ የሚያስችል መርህ ነድፏል ። ይኸውም የሥልጣን ምንጭና ባለቤት ህዝብ ብቻ እንዲሆን የሚያስችል ሥርዓትን መፍጠርና ማዋቀር አስፈላጊነት በመገንዘብ በጋራ/በደቦ/በሕብረት መሥራት የሚለውን ፅንሰ ሐሳብ ላይ በመስማማት የአምባገነንነትን በር እስከ ወዲያኛው ለመዝጋት የሚያስችል መርህ በትክክል አስቀምጧል ።

አሁን ባለንበት ሁኔታ የህዝብ የሥልጣን ምንጭና ባለበትነት በውል ሳይረጋገጥ ፥ ህዝብ የኔ ነው የሚለው ሕገ መንግሥት መኖሩ ብቻ ሳይሆን በዚሁ ሕገ መንግሥት የአስተዳደር ዘርፎችን (ሕግ አፍላቂ ፥ ሕግ ተርጓሚ ፥ ሕግ አስፈፃሚ) ተግባርና ሓላፊነታቸው በግልጽ ተለይቶ ሳይዋቀር ፥ ፖለቲካ ፓርቲዎች ስልጣን ላይ የሚወጡበትና የሚወርዱበት ኣገባብ ተነድፎ ስምምነት ላይ ሳይደረስ፥ ይህንን የሚከታተሉ ተቋሞች (institutions) ሳይመሠረቱ አንዱ ፓርቲ ሥልጣን ቢይዝ እነ ለገሠ እያደረጉት ያለውን አገር አውድም ጥፋት ከማድረስ የሚያግዳቸው ሥርዓት ስለሌለ ካለንበት ኣዙሪት ኣልወጣንም ማለት ነው ። ይህም በመሆኑ የመረጋጋትና የዕድገት ጉዞ ለዘለቄታ ሳይጀምር ትርምስና ብጥብጥ ውስጥ ተመልሰን ልንገባ ነው ። ይህ የሁሉም ዜጋ ጭንቀት የሆነው አገር=ኣድን ጥያቄ መልሱ ለማንኛውም ኣገር ወዳድ ፥ ለቀኙም ይሁን ለግራው ፥ ለለዘብተኛው ይሁን ለአክራሪው ኣንድ ነው። በቅድሚያ ለሁሉም የሚበጅ የጋራ ሥርዓት በጋራ ይዋቀርና ቀጥሎ ህዝብ የፈለገውንና በነጻ ምርጫ የደገፈው ወገን ሥልጣን በደንቡና በአገባቡ ይረከብ ባዮች ነን ። በአገራችን ሰላምና እርጋታ ሰፍኖ ኢትዮጵያ ሁሉም ልጆቹዋ እኩል አቅፋ ዕድገቷ የምናየው በዚህ ሁሉን አቀፍ ፖለቲካዊ ሥርዓት (inclusive politics) ስንገዝ ብቻ ነውና ።

እላይ የተጠቀሱትና ሌሎች ከሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ጋር የተያያዙ በደሎች ባገርና በህዝብ ላይ እየፈጸሙ አሁንም ህዝብ ይመርጠኛል እያሉ በህዝብ የሚቀልዱት እነ አቶ ለገሠ ዜናዊ አሁንም ዕድል አግኝተው ተዝናንተው ሊገዙን ማቀዳቸው ግልጽ ነው። በተጠቀሰው የሪፖርተር እትም "የዘንድሮ ምርጫ በኣሸናፊነት እንደምንወጣ የታወቀ ኣድርገን ወስደን ዋናው ትኩረታችን ምንም ችግር የሌለበት የጠራና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ መሆኑን ሕዝባችንና መላው የዓለም ኅብረተሰብ እንዲያምን ማድረግ ነው።" ይላል ኣቶ ለገሠ። ያልሆነውን ድርጊት እንደሆነ ተደርጎ ማቅረብ እውነትም ያስጨንቃል፥ ግን ይህን ኣስጨናቂ ቅጥፈት ህዝብ ፊት ለማከናወን ሲታቀድ ህሊና ላለው ሰው ኣባባሉ ሁሉ የንቀት ንቀት ነው ። ኣቶ ለገሠ እንዲህ በህዝብና በሃገር እያላገጠ ባለበት ወቅት፥ በተለይ በማመዛዘን ችሎታው ላቅ ባለው ሙሁሩ ወገን የሚታየው መከፋፈልና መሠረታዊ ባልሆኑ ጥቃቅን ልዩነቶች ተጠምዶ ፥ በየጎራው አካኪ ዘራፍ እያሉ መታየት በጣም የሚያሳዝን ከመሆኑ በላይ እነ አቶ ለገሠ ወይም መሠሎቹ እንደገና ተዝናንተው እንዲገዙንና ሀገሪቱን ወደ ባሰ ጉድ መክተት ይሆናል ። ከዚህም አልፎ አንዳንድ ድርጅቶች ህዝቡን የሥልጣን ምንጭና ባለቤት መሆን እንዲችል በቅድሚያ የጋራ ዘላቂ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሕብረት የመመስረቱ ጉዳዩ ሲፈሩትና በተለያየ መልክ ሲቃወሙት ይታያሉ ። በአፍ ለለውጥና ለዴሞክራሲ የቆሙ መስለው ለመታየት ብዙ የሚዘባርቁ፥ በተግባር ግን ይህንን ሥርዓት ለመፍጠር በሚደረገው ርብርብ አንገባበትም ብለው የሚሸሹም አልጠፉም። ግራም ነፈሰ ቀኝ ፍትሕና መብት ተነፍጎት የኖረው ህዝባችን ብዙ አጭበርባሪ አይቶ ተማሮ፥ አሁንስ በቃን የራሳችንን ሥርዓት አዋቅረን እኛ ራሳችን ያመንበት አመራር እንፈጥራለን እያለ ነው። ስለሆነም ለዚህ ጥሪ ምላሽ ለመስጠት ት.ዴ.ትን ጨምሮ 14 ድርጅቶች ህብረት ፈጥረው የህዝቡን ጥሪ እያስተጋቡ በተግባር ለማሳየት ትግሉን ተያይዘውታል ።

በኢትዮጵያችን ለዘላቂ እድገት በር ከፋች የሆነው ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ እውን የሚደረገው ለዚሁ እንቅፋት የሆነው የኣምባገነኑ ለገሠ ዜናዊ ኣፋኝ ሥርአት ሲወገድ እንጂ የሱ ኣጃቢ በመሆን ኣይደለምና ለሃገራዊ ልዕልና ለጋራው እርባና በሕብረት ያቀድነው ክቡር ዓላም እናስቀድም ።

ኣገርን ህዝብ በማስቀደም ኣምባገነንነት ይጠፋል ! !
ትንሳኤ ኢትዮጵያ በሕብረት ይታያል ! !

ት.ዴ.ት. (TAND)

ሕዳር 1997 (Nov.
2004)